የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 36
ADDIS ABABA 20th May, 2013

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፰/፳፻፭ ዓ.ም

ለጐዴ-ቀብሪደሃር አካባቢዎች የገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ..............................ገጽ ፮ሺ፰፻፶፱

CONTENTS

Proclamation No. 788/2013

**Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Rural Electrification Project in Gode–Kebridehar Project Ratification Proclamation ...... Page 6859**

### አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፰/፳፻፭

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለጐዴ-ቀብሪደሃር አካባቢዎች የገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፲ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር (አስር ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.አ.አ ፌብሩዋሪ ፳፰ ቀን ፳፻፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### PROCLAMATION No. 788/2013

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 10,000,000 USD (ten million United States Dollars) for financing the Rural Electrification Project in Gode–Kebridehar was signed in Addis Ababa, on the 28th day of February, 2013;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7th day of May, 2013;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለጐዴ-ቀብሪደሃር አካባቢዎች የገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፰/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ ፌብሩዋሪ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር (አስር ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Rural Electrification Project in Gode – Kebridehar Ratification Proclamation No. 788/2013".

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed in Addis Ababa, on the 28th day of February, 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 10,000,000 USD (ten million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 20th day of May, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት